የረቡዕ ሚያዚያ 11 1998ዓም( አፕሪል 19 2006).

# የፍኖተ ዴሞክራሲ
# ሐተታ

## የሰላሣ አራት ዓመታት የትግል ፅናት

ከሠላሳ አራት ዓመታት በፊት የተጀመረውን ትግል ይዞ የቀጠለው ኃይል፥ ተወደደም ተጠላ፥ ትግሉ ረዘመም አጠረ፥ መስዋዕቱ ከበደም ቀለለ ዓላማውን ከግቡ ሳያደርስ ትጥቁን እንደማይፈታ ከማንኛውም የኢትዮጵያ ጠላት በበለጠ ደህና አድርጎ የሚያውቀውና የሚረዳው ራሱን ህወሓት ብሎ የሚጠራው ቡድን እንደሆነ፥ ፀሐይ የሞቀው ሃቅ ነው:: የውጭ ደጋፊዎቹ ሁሉ የመለስን ቡድን ከተቃዋሚዎቹ ጋር ውይይት እንዲያደርግ በጠየቁት ጊዜ ሁሉ የሚሰጣቸው መልስ፥ ከኢሕአፓ በስተቀር ከሌሎች ጋር ለመወያየት ዝግጁ መሆኑን እነርሱም አይደብቁለትም:: የመለስ አገዛዝ ይህንን መሳይ መልስ መስጠቱ አይፈረድበትም:: መራራውን ትግልና የተከፈለውን መስዋዕት በቀላሉ ረግጦ፥ በተነሣበት ክቡር ዓላማ ላይ መደራደር የማይዋጥለት ኃይል ከመለስ ቡድን ጋር ለውይይት ቢቀርብ፥ ምን ምን ነጥብ እንደሚያነሳ እራሱ ቡድኑ አስቀድሞ ስለሚገባው፥ ይህንን ኃይል የህወሓት መሪዎች ፊት ለፊት ለመቅረብ ድፍረቱም ሆነ አሳማኝ ነጥብ አይኖራቸውም:: ዱባና ቅል አበቃቀሉ እየቅል እንደሆነ ሁሉ ጠባቡ ጥርቅምና ኢሕአፓ በአፈጣጠር፥ በይዘት፥ በዓላማና ግብ የጨለማና የብርሃን ያህል ልዩነት ስላላቸው፥ ቡድኑ ኢሕአፓን የሚፈርጅው በአጥፊና ጠፊ ደረጃ በመሆኑ አያስገርምም:: ኢሕአፓ፥ከእነ መለስ ጋር የመሬት፥ የርስትም ሆነ የድንበር ክርክር የለውም:: ከግለሰቦች ጋር ጠብም ይሁን ፍቅር የመኖርም ጉዳይ አይደለም:: ኢሕአፓ፥እንደነ መለስ በዘር ላይ ለተመሠረተ ፖሊሲ ስለማይታገል ከጠባቡ ቡድን ጋር የዘርም ሆነ የግለሰብ ጥላቻና ችግር የለምበት:: በዚህም ላይ ሊቸግራቸውና ሊጨንቃቸው የሚችለው አሁንም የመለስ ዜናዊን ቡድን ብቻ ይሆናል:: የኢሕአፓ አባላት፥ ከመለስ ቡድን ጋር ያላቸው ችግር፥ መሠረታዊ በሆነው በኢትዮጵያ ሕልውና፥ በሕዝቧ አንድነትና ልዕልና ላይ ነው:: ይህ እስካልተመለሰ ድረስ ትግሉን መጀመር/ መፈጸም የሚባል ነገር አይኖርም:: በሀገር ሉዓላዊነትና አንድነት ላይ ድርድር ብሎ ነገር የለም::

ጭብጥ አሻሮ ይዘህ ስልቻ ሙሉ ቆሎ ወደቋጠረ ተጠጋ በሚለው ስሌት በመመርኮዝ ለዘሌቄታው የኢትዮጵያ ጥቅም ሳይሆን፥ ከጊዜያዊ ድግስ ለመቋደስ ተብሎ ትግሉን ማቋረጥም ይሁን በአጭር መቅጨት፥ ሊታሰብ ባለመታሰቡ ጥያቄው በመጀመርና በመፈጸም ሊታይ አይገባውም:: እኩል የጀመረው ሁሉም እኩል ይፈጽማል ማለት አይቻልም:: መሠረታዊው ጥያቄ ሊሆን የሚችለው፥ የትግሉ ዓላማና ግብ ዕልባት አግኝቷል? ወይስ አላገኘም?

ነው፡፡ ይህ መሠረታዊ ጥያቄ ተገቢውን መልስ እስካለገኘ ድረስ፥ ትግሉን መቀጠል አጠያያቂ ሊሆን አይችልም፡፡ ስለሆነም የትግሉን ፍጻሜ የሚወስነው የዓላማው መሳካት እንጅ የትግሉ መርዘም ወይም የሚጠይቀው መስዋዕት ከባድነት አይደለም፡፡ በአስከፊ ሥርዓቱ ተወዳዳሪ የማይገኝለትን የደቡብ አፍሪካን የነጮችን አፓርታይድ ፖሊሲን ለመገርሰስ ከሰባ ዓመታት የበለጠ ዘመን መጠየቁም፥ የመጨረሻ ግቡ አፓርታይድን አስወግዶ የዜጎቹን መብትና እኩልነት በሚያስከብር ሥርዓት ለመተካት ስለነበር፥ ዓላማው እስኪሳካ ትግሉ መቀጠል ነበረበት፡፡ የዛሬ ሠላሳ አራት ዓመት ትግሉን የቀጠለው ትውልድም፥ አሁንም በፅናት የሚታገለው ከዚህ መሠረታዊና ዓይነተኛ መርኅ በመነሳት ነው፡፡ በመሠረታዊ መርኅ ላይ ያልተገነባ ትግልም መልኅቅ እንደሌለው መርከብ ስለሚዋዥቅ የመሠረታዊ መርኅ ተገዥ መሆን ማለት፥ የትግሉን መጀመሪያና መፈጸሚያ በሚገባ ተረድቶ ትግሉ ዒላማውን እስከመታ ድረስ በፅናት መታገል ማለት ነው፡፡ ይህ መሠረታዊ ሃቅ ለማለስ ዜናዊና ተባባሪዎቹቸ ይረቅቅባቸው እንደሁ እንጅ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ግን፥ የትግል ሀ ሁ ነው፡፡ ያለፉት ጀግኖች አባቶቻችንና እናቶቻችን የኢትዮጵያን ዳር-ድንበር ከውጭ ወራሪ ኃይሎች ጠብቀው ያቆዩት ሳይሰለቹ፥ ሳይበገሩና ሳይንበረከኩ ያለማቋረጥ ሲታገሉ ስለነበር ብቻ ነው፡፡ የስድሣ ስድስቱ አብዮታዊ ትውልድም ይህን አኩሪ ጋሻ አንስቶ በፅናት ትግሉን መቀጠሉ፥ ደግሞ የሀገር ወዳድነት ቅርስ መተላለፉን አረጋግጧል፡፡

ይህ መሆኑ የሚያስደንቅ አይሆንም፡፡ ሊያስገርምና ሊያሳዝን የሚችለው የተነሳበትን ክቡር ዓላማና ሀገራዊ ቃል-ኪዳን ዘንግቶ ተፍረክርኮ ቢቀር ነበር፡፡ በሌላ አኳያ ሲታይ ደግሞ፥ በየጊዜው እንደ ሁኔታው እንደ እንጉዳይ በቅለው የሚጠፉት ድርጅቶቹም የነበራቸውና ያላቸው ከባድ ችግር የፖለቲካ ትግል ውጤት በአንድ ቀን ጀምበር የሚገኝ ስለሚመስላቸው ጭምር ነበር/ነውም፡፡ ትግል ከጡረታ በኋላ የሚመስላቸውና ሁኔታ እየተጠበቀ በወረት የሚካሄድ እየመሰላቸው ብቅ ጥልቅ እያሉ የሚብተከተኩ ክፍሎች፥ ሁልጊዜ የማይገነዘቡት ዓቢይ ጉዳይ ቢኖር፥ ኢትዮጵያን ቀስፎ ከያዛት ጥልቅና መሠረታዊ ችግር ነፃ ለማውጣት የሙሉ ሕይወት ትግልና ታላቅ መስዋዕት ማስፈለጉን ነው፡፡ ትግሉን ከዳር ለማድረስ በግድ ሳይታክቱ፥ ሳይደክሙ፥ ማቄን ጨርቄን ሳይሉና ለማንኛውም ፈተናና ችግር ሳይንበረከኩ በቀጣይነት መታገልን ይጠይቃል፡፡ የተጀመረው ትግል ዓላማው የተሳካ ሆኖ ግቡን እንዲመታ ካስፈለገ፥ ቆራጥና የማይታክቱ ታጋዮች ወሳኝ ሚና አላቸው፡፡ ፈጣንና ተለዋዋጭ በሆነ ሁኔታ ውስጥ እንደ መስቀል ወፍ ብቅ ብሎ ለመክሰም ትግል እናካሂዳለን ብሎ መባከን ከአንድ ቀን ሰላማዊ ሰልፍ ዳንኪራና የስሜት ማስተንፈሻ እፎይታ አያልፍም፡፡ ኢትዮጵያን ከዘረኝነት አገዛዝ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ነፃ ለማውጣት፥ በግድ ኢትዮጵያዊ አይበገሬነት ባሕርይና ቆራጥነት ያስፈልጋል፡፡ ይህ ደግሞ ለሁሉም ተሟልቶ እንደማይሰጥ ያለፈው ሠላሳ አራት ዓመታት የትግል ተመክሮ ሕያው ምሥክር ሆኗል፡፡ ደራሲ ከበደ ሚካኤል አዝማሪና የውሃ ሙላት በተሰኘው ግጥማቸው አንድ ስንኝ ውስጥ “ያልሰማው ሲመጣ የሰማው ሲሄድ” እንዳሉት በዚህ የሠላሳ አራት ዓመታት የትግል ሂደት ውስጥም አፍለኛው ሲመጣ፥ የሰለቸው ሲሄድ መመልከት

የተለመደ ክስተትና ትዝብት ሆኗል። ምንም እንኳን ትውልዱ ሁሉም በጠቅላላ ይህን ይጋራዋል ባይባልም፥ ይህ ደግሞ የአያሌ ሺ ዓመታት የበለፀገ ታሪክና ባሕል ካለው ሕዝብ አብራክ የወጣ ትውልድ ባሕርይ ሊሆን ባልተገባው ነበር። ያም ሆነ ይህ፥ የተጀመረው ትግል ዓላማውን እስከመታ ድረስ አስፈላጊው መስዋዕት እየተከፈለ እንደሚቀጥል እንኳንስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀርቶ ጠላቶቹም ቢሆኑ ያለመጠራጠር ይቀበሉታል። ጀምሮ መተውና ፀንቶ መፈጸም የሰማይና የምድር ያህል ርቀት ስላላቸው፥ ጀምረው የተዉትን ጸንተው ለመፈጸም የቀጠሉትን ቢያንስ እንቅፋት ከመሆን ቢወስኑ ትግሉን እንደደገፉት ይቆጠርላቸዋል። በዚህ ባሳለፍነው ሳምንት መጨረሻ አራተኛ ጉባዔውን እጅግ በተሳካ ሁኔታ አጠናቅቆ የተነሳው ኢሕአፓ፥ የወደፊት ትግሉን በሁለገብ መልኩ የሚያፋፍም መሆኑን በማያወላውል ሁኔታ ሲወስን፥ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የገባውን ቃልኪዳን እንደገና በማደስ ነው።

በፅናትና በህብረት ለሕዝብና ለህገር ክብር እንታገል!!